# በቶሮንቶና አካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን 113ኛውን የአድዋ ድል በአል አከበሩ፣ በኢትዮጵያም የሰብአዊ መብትና የህግ የበላይነትና እንዲከበሩ ጠየቁ

*የኢትዮጵያ ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው በየአመቱ ከጥቁር ህዝቦች ታሪክ ወር ጋር የሚገጥመውን የአድዋ በአል በደማቅ ሁኔታ ፌብሩዋሪ 28፣ 2008 አክብሯል:: የኦንታሪዮ ምክትል ጠቅላይ ሚንስትርና እንዲሁም የኢንዳስትሪና ሃይል ማመንጫ ሚኒስትር ሚስተር ጆርጅ ስሚዘርማን፣ የኒው ደሞክራቲክ ፓርቲ ተወካይ ሚስ አንድርያ ማፋት፣ በተጨማሪም፣ የኢትዮጵያውያን ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ቡሻ ታአና የማህበሩ ዋና ፀሃፊ አቶ ዮናስ ታደሰ፣ እንዲሁም የአዛውንቶችና የወጣቶች ተወካዮች በአሉን በማስመልከት ሰፋ ያለ ንግግር አድርገዋል::*




*በቶሮንቶ የኢትጵያውያን ኮሚኒቲ ጋር በቅርብ የሚሰሩትና የኢትዮጵያውያንን በአል በተከታታይ የሚሳተፉት ሚስተር ስሚዘርማን የአድዋ ድል የጥቁር ህዝቦች ሁሉ ታሪክና ድል መሆኑን ካብራሩ በኋላ፣ የኢትዮጵያን የረጂም ጊዜ የነጻነት ተጋድሎን አድንቀዋል:: ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያን ከውጭ ወራሪዎች ያስመዘገቡትን ነጻነት በሃገርቸው በተለያዩ ጊዜ ባስተዳደሩቸው አምባገነን መሪዎች ምክንያት የነጻነታቸውና ሙሉ ለሙሉ ተተቃሚዎች እንዳልሆኑ በማስገንዘብ፣ በተለይም በሰብአዊ መብት ረገጣና በዲሞክራሲ እጦት የኢትዮጵያ ህዝብ ከፍተና በደል እየደረበት እንድሆነም አስምርውበታል:: በዚህ አጋጣሚ ወ/ት ብርቱካን በአስቸኳይ እንድተፈታ የሚጠይቀውንና ለጠቅላይ ሚኒስተር ስፐሀን ሃርፐር የሚላከውን ፐቲሽን እንድፈርሙና ሌሎችም የሳቸውን አራያ ተከትለው ድምሳቸውን ለ ፓርላማ አባላቶቻቸው ሁል እንዲያደርሱ ተማጽነዋል::*

*የኒው ዴሞክራቲክ ፓርቲ ተወካይ የሆኑት ሚስ አንድረያ ስለ ኢትዮጵያውያን በአድዋ ስለተጎናጸፉት ድል ሰምተው እንደማያውቁና በተለይም ይህን የጥቁሮች ታሪክ በትምህርት ቤት እንኳን እንዳልተማሩት ገልጸው፣ በዚህ በአል ላይ በመገኘታቸውና የማያውቁትን የኢትዮጵያ በተለይም አኩሪ የጥቁሮች ታሪክ በመማራቸው የተሰማቸውን ደስታ ገልጸው፣ ነገር ግን በአሁን ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚፈጸመው የሰብብአዊ መብት ረገጣና የዲሞክራሲ አለመኖር ከመናገር አልሸሸጉም:: በዚህ አጋጣሚ ሚስ አንድሪያ ትውልደ ኢትዮጵያ ካናኔድያውያን አዲስ ያገኙትን የፖሌቲካ መብት ተጠቅመው፣ በተለይም በፖሌቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ተሳትፏቸውን እንዲያሳድጉ አሳስበዋል::*




ዶ/ር ቡሻ ታኣ በቶሮንቶና አካባቢው የኢትዮጵያውያን ማህበር ፕሬዚዳንት ማህበሩ የጥቁር ህዝቦች ታሪክ መከበሪያ የሆነውንና፣ ጀግና አያቶቻችን ከፍተኛ መስዋእትነት የከፈሉበትን የአድዋ ድል  ማህበሩ ላለፉት 13 አመታት በማክበር፣ማህረሰቡ በሃገሩ ታሪክ እንዲኮራ፣ አዲሱ ትውልድም የውላጆቹን አገር ታሪክ እንዲማር ለማድረግ በመጣር ላይ መሆኑን ገልጸዋል:: አያይዘውም ይህንን አኩሪ የኢትዮጵያ ታሪክ ማህበርሰቡ ጊዜ ባመጣው የዘር ክፍፍሎሽ ሳይሆን ኢትዮጵያውያን በአንድነት  ለሰብአዊ መብት መከበር፣ ለህግ የበላይነትና፣ ለነጻነት ከመቸውም ጊዜ በላይ ተባብረን መስራት አለብን ሲሉ ገልጸዋል:: በተከታታይም የወጣቶች ኮሚቴ ተወካይ የአድዋ ድል ወጣቱ ትውልድ እንዴት እደሚኮራበትና በጥቁር ህዝቦች የነጻነት ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባው አስረድታለች::

የአዛውንቶችን ኮሚቴ ተወካይ አቶ ትእዛዙ መጫ  ስለ አደዋ ታሪክና ገድል ከዓባቶቻችን አንደበት በማለት ይህንን ቀን ለምን አዲሱ ትውልድ ማክበር ማሰብና እንዲሁም ሊኮራበትና ሌሎች ሁሉ ማስተማር እንዳለበት በሰፊወ አብራርተዋል::




የኢትዮጵያ ታሪክ በአብዛኛው የጦርነት ታሪክ ነው በማለት የጀመሩት ሌላው የእለቱ ተናጋሪ አቶ ዮናስ ታደሰ ናቸው:: ከቱርኮች፣ ከሱዳን ማህዲስቶች፣ ከግብጽ፣ ከእንግሊዝና ጣሊያኖች ጋር ኢትዮጵያ ውያን የነጻነት ተጋድሎ ማድረጋቸው አውስተው ኢትዮጵያ በጦረኝነት የፈጠረቻቸው ሳይሆን፣ ነጻነቷን ገፊው ህዝቡን አንበርክከው የቅኝ ገዢነት ሰንሰለታቸውንና

*እግር ብረታቸውን ሊቸንክሩባት ቆርጠው የተነሱ የወራሪ መንግስታት ፈታኞች ያመጡበት መከራና ፈተና ነበር ብለዋል:: የአድዋ ድል ለነጮቹ መጥፎ የታሪክ ጠባሳ የሆነውን ያህል ለሰብአዊ ክብራቸው ይታገሉ ለነበሩ ጥቁር ህዝቦች የነጻነት ጎህ የቀደደ በአርያነቱም ለዘለአለም የሚኖር መሆኑን አስረድተዋል::*

*አቶ ዮናስ በመጨረሻ ንግግራቸው አያቶቻችን መስዋት ሆነው ያስለቀሉን አገራችን ኢትዮጵያ አንድነቷም ሀነ የህዝቦቿ ነጻነት ከመቸውም ጊዜ የከፋ መሆኑን በአጽንቶ ገልጸው፣ የኢትዮጵያውያን ማህበር በቶሮንቶ በመተዳደሪያ ደንቡ የታቀፈውን በምንኖርበት አገር ካናዳ በህገ መንግስቱም ሆነ የመብትና ነጻነት ቻርተር የተደገፈውን የሰብአዊ መብት ጥሰት በማናቸውም ጊዜ እንደሚያነሳ አስረግጠው፣ በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ጥሰት ሰፈጠርና ይህም በአለም አቀፋዊና ሃገራዊ የሰባዊ መብት ተሚጋች ድርጅቶች ሲረጋገጥ ከማህበረሰቡ አባላትና በውስጡም ከሚገኙ የተለያዩ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት ተቋማትን አሰተባብሮ ባዋቀረው ኮሚቴ በኩል ቅሬታውንና ተቃሞውን ለካናዳም ሆነ ለሌሎች ለጋሽ አገሮች የማሰማቱን ተግባር ከአሁን በፊት ሲያከናውን የነበር ተግባር እንደሆነና ወደፊትም እንደሚቀጥልበት በሰፊው አስረድተዋል::*

*በበአሉ ላይ አርቲስት ማርታ አሻጋሪ፣ እሸት፣ ምኒልክና ሂሩት አዝናኝና ወቅታዊ ዜማችን እንዲሁም የአድዋ ድልን ገድለ በተመለከተ ግጥም በማቅረብ ለበአሉ ከፍተኛ ድምቀት ሰጠውታል::*

---

በተከታታይ በሃገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አስተዳደር የሚደርሰውን የሰብአዊ መብት በደልና የህግ የበላይነት ያለመኖር፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ቶሮንቶና አካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ስነ ልቦና መጉዳቱን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ የኢትዮጵያውያን ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው አንድ ወጥ የሆነ ከሁሉ የማህብረሰቡ አባላትና ድርጅቶችን ያካተተ አንድ የስብአዊ መብት ተቆርቋሪ ኮሚቴ አውቅሯል:: ይህም ኮሚቴ ማርች 2፣ 2008 ስለሚካሄደው አለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብትና የፍትህ ህዝባዊ ሰልፍ ድጋፍ ይህንን የድጋፍ መግለጫ አውጥቷል::

## የአቋም መግለጫ

1. በኢትዮጵያ ውስጥ ለህሊናቸው ተገዥ በመሆናቸው ብቻ እንደ ወንጀል ተቆጥሮባቸው በየእስርቤቱ የሚማቅቁት የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር ብርቱካን ሚደቅሳ፣ አርቲስት ቴዎድሮስ ካስሁን(ቴዲ አፍሮ)፣ ጸጋየ ገብረመድህን(ደብተራው)እንዲሁም በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የህልና እስረኞች ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ እንጠይቃለን::

2. ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. በስልጣል ላይ ለመቆየት ያለውን ፍላጎት ብቻ ለማሳካት ሲል ራሱ ያወጣውን ህገ መንግስትና ህግ እንደሚስማማው አድርጎ እየተረጎመ የፖሌቲካ ተቃዋሚዎቹን ባልተስተካከለ የዳኝነት ኃል እየነረተ ለእስር መዳረጉን በአስቸኩዋይ እንዲያቆም እንጠይቃለን

3. ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ለዴሞክራሲያዊ አሰራር መስፈን ህዝቡ ያለውን ፍላጎት ተገንዝቦና ለዚህም እውን መሆን በሰላማዊ ትግል የተሰማሩ የፖሌቲካ መሪዎችንና ድርጅቶችን ማዋከቡንና ማሳደዱን አቁሞ ለዴሞክራሲዊ አሰራር ግንባታ እንደ ፓሪቲ ግዳጁን እንዲወጣ እንጠይቃለን::

ማርች 01፣ 2009